# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 169 ነሃሴ 5 2003 ገጽ 1

**ቢቢሲ እስካሁን ይፋ ያላደረጋቸው መረጃዎችን እንዲያወጣ እና በጀመረው መንገድ የሃቅ ማፈላለግ ጋዜጠኝነትን እንዲቀጥል ጥሪያችን ማቅረብ፤ ሌሎች ዓለም ዓቀፍ የዜና አውታሮችም ተመሳሳይ የሃቅ ማፈላለጉን ሥራ እንዲያደርጉ መገፋፋት ይገባናል። በየአገሩ የተበተኑ ኢትዮጵያዊያን ተሰባስበን የቢቢሲን መረጃዎች በመያዝ በየምንገኝባቸው አገሮች መንግሥታት ላይ ጫና ማድረግ ይኖርብናል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የኦነግና ኦብነግ ህብረ ብሄር ከሆነው ግንቦት 7 ጋር ህብረት ፈጥሮ ጸረ ወያኔ ትግል ለማካሄድ ንግግር መጀመር የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ አደጋ ላይ እየጣለ ነው ተባለ

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ በኦሮሚያና በኦጋዴን ክልል ተዘዋውሮ ባሰባሰበው የህዝብ አስተያየት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በህዝቦች መካከል ጥላቻንና አለመተማመንን በመፍጠር የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም ሲል አማራን ወራሪና ጨቋኝ ሌላውን ተወራሪና ተገዥ አድርጎ እንዳይቀራረብና እንዳይነጋገር የገነባው የጥላቻ ድልድይ እየተሸረሸረ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሎአል። በሁለቱም ክልሎች ተወላጆች ከሆኑ የመካከለኛ የትምህረት ደረጃና ከዚያም በታች ካላቸው በርካታ ሰዎች የተሰባብሰበው አስተያየት እንደሚያመለክተው እስከ ምርጫ 97 ድረስ ኢትዮጵያ የምትባለውን አገር የፈጠረው አማራ እንደሆነና በአገሪቱ ውስጥ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረው የፍትህ፤ የእኩልነትና የነጻነት እጦት በአማራ ላይ ሲላከክ እንደቆየ በዚህም ምክንያት ስለ ኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ብሄራዊ ጥቅም መቆርቆር ወያኔ የጣለውን አደሃሪ ሥርዓት መልሶ እንደመናፈቅ ተደርጎ በወያኔ ባለሥልጣናትና በካድሬዎቻቸው ሲወገዝ መቆይቱ ታውቆአል። ሆኖም በአገሪቱ መከላኪያ፤ ደህንነትና ፖሊስ ሠራዊት ከፍተኛ አዛዥነት ቦታዎች እንዲሁም በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ በግልጽ እየታየ ከመጣው የትግራይ ብሄረሰብ የበላይነት በተጨማሪ በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት የፖለቲካውን ሥልጣን የሚዘውሩት የአንድ ክልል ተወላጅ የህወሃት አባላትና ዘመዶቻቸው በአንድ ጊዜ ዲታ ሆኖ መውጣት "ከነፍጠኛው የአማራ ጭቆና በትግላችን አላቀናችኋል" ለሚባሉት የአገሪቱ ጭቁን ብሄር ብሄረሰቦች የሚዋጥ አልሆነም። በአንጻሩ የአማራ ሥርዓት ይባል በነበሩት ቀደምት ሥርዓቶችና በአሁኑ የወያኔ ሥርዓት መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት በብሄር ላይ የተመሰረተ አድልዎ ምንም እንደሚመስል ህዝብ እንዲያውቅና እንዲፈርድ አስችሎታል ተብሎአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአለማቀፍ ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ የሚለግሱት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላር ለፖለቲካ ጭቆና እንደመሳሪያነት ሲያገለግልና ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲካሄድበት እያዩ እይቶ እንዳላየ በመሆን የእርዳታ እጃቸውን ማስፋታቸው አግባብ እንዳልሆነ ቢቢሲ ገለጠ

በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የመብት ረገጣና የፖለቲካ አፈና ለመቃኘት ቢቢሲ ወደ ኢትዮጵያ በስውር አስገብቶ የነበረው ጋዜጠኛ አንገስ ስቴክለር ባለፈው ሃሙስ ሃምሌ 29 ቀን 2003 ለአለም ህዝብ ይፋ ባደረገው የምርመራ ሪፖርቱ፤ እንግሊዝን ጨምሮ በርካታ የምዕራብ አገር መንግሥታት ለኢትዮጵያ የሚሰጡት ገንዘብ የፖለቲካ ተቀናቃኞችን ለማጥፋትና ዜጎችን ለማፈን አገልግሎት ላይ እየዋለ መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ አጋለጠ።

እንደ ቢቢስ ሪፖርት ኢትዮጵያ ውስጥ ተገዶ መደፈር ቶርቸርና ሆነ ተብሎ ለረሀብ ጠኔ መዳረግ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እየደረሰባቸው ያለ ግፍና መከራ መሆኑ እየታወቀ አለም አቀፍ ለጋሾች ችግሩን አይተው እንዳላዩ ከወያኔ አገዛዝ ጋር ሽርክናቸውን አጠናክረዋል።

በኢትዮጵያ የተለያዩ ግዛቶችና በጎሬቤት ኬንያ ያለውን ሰቆቃ ቃኝቶ የተመለሰው ጋዜጠኛ አንገስ ስቴክለር በየቀኑ ረሀብና ድርቅን በመሸሽ በሚሊዩን የሚቆጠሩ ስደተኞች ከኢትዮጵያና ሶማሊያ ወደ ሰሜን ኬንያ የስደተኞች ካምፕ ጋዳፕ እንደሚተሙ መመልከቱን ዘግቦአል።

ጋዳፕ በተባለው በዚህ ካምፕ ውስጥ ከ 400,000 በላይ ስደተኞች ሲኖሩ የኢትዮጵያውያን ስደተኘች ቁጥር ከእለት እለት እየጨመረ እንደሚገኝ ነው የቢቢሲ ኒውስ ናኢት ዘጋቢ የገለጠው።

በወያኔ አሰቃቂ ቅጣት ሰለባ ከሆኑት ሴቶች መሃል አንዳ የተባለች የኦጋዴን ክልል ተወላጅ አገዛዙ በክልሉ ያሠፈረው ጦር ያለአግባብ እንዳሰራትና የስምንት ወር ነፍሰጡር መሆኗ እየታወቀ ከአንድ በላይ በመሆን አስገድደው እንደደፈሯት እና እንደደበደቧት በዚህም የተነሳ ጽንሰዋ እንደተጨናገፈ እና ከመጠን በላይ የሆነ ደም እንደፈሰሳት የሰጠቿውን የምስክርነት ቃል ጋዜጠኛው ዘግቦታል። "በመንግስትና በተቃዋሚዎች መካከል ግጭት በተፈጠረ ቁጥር የወያኔ ወታደሮች ቅርብ ከተማ ወደሆነው በመሄድ ሰላማዊ ነዋሪዎችን መግደልና ማሰራቸው ተለመደ ጉዳይ ነው" በማለት ለጋዘጠኛው ከተናገሩት አንዷ የአራት ልጆች አያት ነበሩ የሳቸውንም ወንድ ልጅ አይናቸው እያየ ፊትለፊታቸው ህይወቱን እንደቀጠፉትና እሳቸውንም በመቶዎች ከሚቆጠሩ ሰዎች ጋር ወደ ወህኒ በማውረድ ለአንድ አመት ከስድስት ወር በእስር ቤት ማቆየት ብቻ ሳይሆን፣ በየለሊቱ ሰውነታቸው ጠፍረው በመያዝና በማሰር እየተፈራረቁ የአስገድዶ መደፈር ጥቃት እንዳደረሱባቸው በምሬት ገልጠዋል።

ሌላዋ ተመሳሳይ እጣ የደረሳት የሴት ልጅ እናት፣ በዚህ ሁኔታ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ የዋጋ ንረትን መቆጣጠር አልተቻለም፣ የእቃዎች ዋጋ ከአምናው ጋር ሲተያይ የ50 በመቶ ጭማሪ አሳየ

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት በቢሊየኖች የሚቆጠር ዶላር እንደዘረፉና እየዘረፉም እንደሆነ በተደጋጋሚ እየተነገረላት ባለው ሃገራችን ኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት አምና ከነበረበት ወደ 50 በመቶ ከፍ ማለቱን የዘረኛው አገዛዝ ማእከላዊ ስታትስቲክስ ጽ/ቤት በይፋ መግለፁ ታወቀ።

ብሉምበርግ በመባል የሚታወቀው አለም አቀፍ የዜና አውታር ባወጣው በዚሁ ዘገባው የምግብ ዋጋ ባለፈዉ ወር ከነበረበት 45.3 በመቶ ወደ 47.4 በመቶ ማደጉን የገለጸ ሲሆን ሮይተርስ የዜና ወኪል በበኩሉ የዋጋ ግሽበቱ መሰረታዊ ምክንያት ከፍጆታ እቃዎች 57 በመቶ በሚሆነዉ በጥራጥሬ እህሎች ፤ በዘይት፤ ቅባትና እንዲሁም ቅቤና ወተት በመሳሰሉት የእንስሳት ተዋፅኦ ላይ የታየዉ የምግብ ዋጋ ጭማሪ እንደሆነ አስታዉቋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በዚህ አመት በ7.5 በመቶ እድገት ያሳያል የሚል ግምት ቢኖርም የዋጋ ግሽበት የአገሪቱ ፈታኝ የኢኮኖሚ ችግር እንደሆነ የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት /አይ ኤም ኤፍ/ የሚያምን መሆኑን ሮይተርስ በዘገባዉ ገልጿል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የቪ ኦ ኤ ዜና ዘጋቢ የሆነው ፒተር ሃይላይን እንደገለጸው "ውድ እንደሆነ ነው ሸማቾች የሚናገሩት። በአንድ ወቅት የአትክልት ዘይት በ20 ብር ይሸጥ ነበር፤ አሁን በሊትር ስልሳ ብር ገብቷል። የ200 እጅ ጭማሪ መሆኑ ነው። ያው ሸማቾች ከኪሳቸው ጋር ፍላጎታቸውን ያስተካክላሉ። የአትክልት ዘይት ሲወደድ የዘንባባ ዘይት መግዛት ጀምረዋል" ብሉአል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሱዳን በተባበሩት መንግስታት ሄሊኮፕተር ላይ ጥቃት ልትፈጽም ሙካራ ማድረጉአ ተዘገበ

ሱዳን ውስጥ በአቢየ ግዛት ቀደም ብሎ የተቀበረ ጸረ ሰው ፈንጂ ፈንድቶ የአራት ኢትዮጵያዊያን ወታደሮችን ህይወት ባጠፋበት ወቅት በፍንዳታው የቆሰሉ ወታደሮችን ለህክምና ርዳታ ለማድረስ ጥረት በማድረግ ላይ የነበረ ሄሊኮፕተር በሱዳን ወታደራዊ ሃይል ጥቃት ሊፈጸምበት ሙከራ ተደርጎ እንደነበር ቢቢሲ የዜና አውታር ባወጣው ዘገባ ላይ አመልክቱአል።

ሱዳን ውስጥ አቢየ ግዛት የሚገኙ የተባበሩት መንግስታት ባለስልጣን አላይን ሌ ሮይ ለቢቢሲ እንደገለጹት የተባበሩት መንግስታት ሄሊኮፕተር በፍንዳታው የተጎዱ ቁስለኞችን ለመርዳት በስፍራው በደረሰበት ወቅት የሱዳን የጦር ሃይል ተኩስ ለመክፈት ሙከራ በማድረግ ላይ እንደነበር የታወቀ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ቁስለኞችን ከስፍራው ለማንሳት ከሶስት ሰአታት በላይ ጊዜ የወሰደ መሆኑ ታውቅቁአል።

እንደ ባለስልጣኑ ሪፖርት ሄሊኮፕተሩ ቁስለኞችን ማንሳት ባለመቻሉና ሄሊኮፕትሩም ካረፈበት ቦታ እንዲነሳ ከሱዳን የጦር ሃይል ጋር ውይይት እየተካሄደ በነበረበት የሶስት ሰአታት ጊዜ ውስጥ የሶስቱ ወታደሮች ህይወት ሊያልፍ መቻሉን ገልጸዋል፣ ፣ እንደ ቢቢሲ ዘገባ የተቀበረ ጸረ ሰው ፈንጂ ሲፈነዳ ወዲያዉኑ ህይወቱ ያለፈው አንድ የኢትዮጵያ ወታደር ብቻ እንደነበር ነገር ግን ሶስቱ ተጨማሪ ወታድሮች ህይወታቸው ያለፈው ከተወሰኑ ሰአታት በሁአላ መሆኑ ታውቁአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በአገር ውስጥ ምንም አይነት ነጻ ሚዲያ እንዳይኖር የመለስ በረከት አገዛዝ የሚከተለውን አቋም አጠናክሮአል

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ብሮድካስት ባለሥልጣን በመጪው ዓመት ለአዲስ የግል ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ ፈቃድ ለመስጠት እቅድ እንደሌለው መግለጹን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ላይ አመለከተ። ዘጋቢያችን በሃገር ውስጥ የሚታተመውን አዲስ አድማስ ጋዜጣ ዋቢ በማድረግ በላከልን ዘገባ የባለሥልጣኑ አንድ ሐላፊ በ2003 ለግል ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ የጠየቀ የለም። ስለዚህ መሥሪያ ቤቱ በመጪው ዓመት የሬዲዮና ቲቪ ፈቃድ ጠያቂዎች ቢመጡ እንኳን "ፈቃድ የመስጠት እቅድ የለውም።" በማለት መናገሩን ገልጹአል። ጋዜጣው አያይዞም በተገባደደው ዓመት ለ11 ጋዜጦች እና ለ31 መጽሔቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሰጥተናል በህትመት ሚዲያ ዘርፍ "ፈቃድ ጠይቆ የተከለከለ የለም" በማለት የተለመደውን ወያኔያዊ ቅጥፈት መናገሩ ታውቁአል።

ይህን የብሮድካስት ባለስልጣን ውሳኔ አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ ህትመቱን ያቁዋረጠ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ በሰጡት አስተያየት ኢትዮጵያ ውስጥ ነጻ ፕሬስ የሚባል ከሞተ ቆይቱአል። አንዳንድ ውን ውን የሚሉ ጋዜጦችም ቢሆኑ ህልውናቸው ፈተና ላይ ከወደቀ መቆየቱ ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ይህ እንግዲህ በጋዜጦች ላይ ነው። ወደ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስንመጣ ከመጀመሪያውም ነጻ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ የሚባል ነገር በአገራችን እንደለሌና እንዳይኖርም ፍቃድ ስከለከል ኖሮ ያልነበረን ነገር ከለከልን ማለት ትርጉም የለውም። የልቁንስ የሚያሳስበው ነገር እንዲህ አይነቱ ቅጥ ያጣ ህገወጥ ተግባር እስከመቸ ድረስ መቀጠል ይኖርበታል የሚለው ነው። እናም በኔ እምነት ኢትዮጵያዊያን ምንም የመረጃ አማራጭ ሳይኖራቸው በወያኔ ፕሮፓጋንዳ ጆሩአቸውን ከማደንቆር ነገ ዛሬ ሳይሉ ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት መታገያ ጊዚያቸው አሁን ነው ብለዋል።

ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ በሃገር ውስጥ ከሚተላለፉ የዜና አውታሮችና ጋዜጦች አፈና በዘለለ መልኩ ከውጪ ሃገራት በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፉ ሬዲዮ ጣቢያዎችን ማለትም የግንቦት ሰባት ሬዲዮን ጨምሮ የ ቪ ኦ ኤ፣ የጀርመን ሬዲዮና ሌሎችንም፣ እንዲሁም በአይነቱና በይዘቱ ልዩ የሆነውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳትን ስርጪት ለማገድ በየቀኑ በሚሊየኖች የሚቆጠር የህዝብ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

## ቢቢሲ: ስቃያችንን ለመታዘብና ለማጋለጥ በመድፈሩ እናመሰግናለን፤ መንግሥታትም ዓይኖቻቸውን ይግለጡ!!!

በመላው ዓለም ከፍተኛ ተሰሚነት ካላቸው የዜና አውታሮች አንዱ የሆነው የብርታኒያ የዜና አውታር (ቢቢሲ) ሰሞኑን ስለኢትዮጵያዊ ያወጣው ዘገባ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል። ቢቢሲ ኢትዮጵያዊያን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ የምናቀርበውን ወቀሳ ራሱ ለማጣራት ወስኖ ጋዜጠኞቹን በሽፋን ወደ ኢትዮጵያ ከተሞችና ገጠሮች አስገባ መረጃዎችን ሰበሰበ። የተበዳዮችን ምሬት እመንደራቸው ድረስ በመሄድ ሰማ፣ አየ።

ከሁሉ አስቀድሞ ቢቢሲ የነፃ ሚዲያ ሚናን በአርዓነት ባጎለበተ መንገድ መረጃዎችን ከምንጫቸው ለማግኘት ስላደረገው ጥረት ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አድናቆቱንና ምሥጋናውን ያቀርባል።

የቢቢሲ የሃቅ ማፈላለግ ጋዜጠኝነት የተሳካ እንደነበር "በኢትዮጵያ እርዳታን ለፓለቲካ አፈና መጠቀም" በሚል ርዕስ ሰሞኑን ካቀረበው ዘገባ መረዳት ይቻላል።

ጋዜጠኞቹ በኦጋዴን፣ በባሌ፣ በወላይታ፣ በደቡብና ምዕራብ ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ በመዘዋወር ኢትዮጵያዊ ድሃ እየደረሰበት ያለው ዘግናኝ ሰቆቃ በገዛ ዓይኖቻቸው ተመልክተዋል። በተለይም:-

- የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታን ሳይጨምር ለልማት እየተባለ ከምዕራባዊያን በየዓመቱ የሚጎርፈው 3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለትም አምሳ አራት ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር (ብር 54, 000, 000, 000) መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ እንደፈለጉ እንደሚያዙበት አረጋግጠዋል፤
- መለስን አልደገፉም የተባሉ ነዋሪዎች መሰረታዊ የሆኑ የምግብና የውሃ አቅርቦት እርዳታ መነፈጋቸውና በዚህም ምክንያት አዋቂዎች ሳይቀር በረሃብ መሞት መጀመራቸው ቦታው ድረስ በመሄድ በዓይኖቻቸው አይተዋል፤
- መለስን ያልደገፉ ገበሬዎች ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር እንደማያገኙ ከገበሬዎቹ አንደበት ሰምተዋል፤
- ወጣት ሴቶች ብቻ ሳይሆን በእድሜ የገፉ እናቶች፣ አያቶች፣ ነፍሰጡሮች ሳይቀር በወታደሮች መደፈራቸውን ከበደሉና ግፉ ቀማሾች አንደበት ሰምተዋል፤ የተበዳዮችን ጠባሳዎች ተመልክተዋል፤
- ሰቆቃ የተፈፀመባቸው፤ ተዘቅዝቀው የተሰቀሉ፣ ብልታቸውን የተኮላሹ ወንዶችን አነጋገረዋል፤
- በአጠቃላይ ለመስማት የሚሰቀጥጡ ግፎችን ሰምተዋል፣ አይተዋል ።

ጋዜጠኞቹ ይዘው ከመጡት ሰፊ የመረጃ ክምችት አንፃር ሰሞኑን ያቀረቡት ዘገባ "ለቅምሻ" ያህል የለቀቁት መሆኑን በድረገፃቸው ፍንጭ ሰጥተዋል።

በቢቢሲ ዘገባ ሳቢያ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ዓለም ዓቀፍ ውግዘትና መገለል እንዲደረግበት ለማድረግ የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል። ቀድሞ እኛ ኢትዮጵያዊያን እነዚሁኑ ሃቆች ስንናገር አሜሪካዊያንና አውሮፓዊያን ለማመን ይቸገሩ ነበር ይሆናል።

አሁን ግን የራሳቸው ሰዎች በዓይናቸው ለመመልከት ችለዋል፤ ደፍረውም ተናግረውታል። ይህ በራሱ ትልቅ ድል ነው። ሆኖም ግን በዚህ መቆም የለበትም። የቢቢሲ ዘገባ ተጨማሪ ዘገባዎችን ማስከተል እና ተጨባጭ ውጤቶችን መፍጠር መቻል አለበት። ይህን ማድረግ ያለብን ደግሞ እኛ የጉዳዩ ባለቤቶችና ተጠቂዎች የሆንን ኢትዮጵያዊያን ነን።

ቢቢሲ እስካሁን ይፋ ያላደረጋቸው መረጃዎችን እንዲያወጣ እና በጀመረው መንገድ የሃቅ ማፈላለግ ጋዜጠኝነትን እንዲቀጥል ጥሪያችን ማቅረብ፤ ሌሎች ዓለም ዓቀፍ የዜና አውታሮችም ተመሳሳይ የሃቅ ማፈላለጉን ሥራ እንዲያደርጉ መገፋፋት ይገባናል። በየአገሩ የተበተኑ ኢትዮጵያዊያን ተሰባስበን የቢቢሲን መረጃዎች በመያዝ በየምንገኝባቸው አገሮች መንግሥታት ላይ ጫና ማድረግ ይኖርብናል። መንግሥታቱ ከምን አይነት አገዛዝ ጋር ተሻርከው የድካማቸውን ውጤት በምን ዓይነት እኩይ ተግባር ላይ እያባከኑ መሆኑን ለህዝብ ማሳወቅ የትግላችን አንዱ አካል ማድረግ ይኖርብናል።

ኢትዮጵያውያን በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ እየደረሰብን ያለውን በደል ለመዘገብ ቢቢሲ ያደረገውን ጥረት እናደንቃለን፤ ሌሎች የዜና አውታሮች ተመሳሳይ ተግባር እንዲከውኑ ጥሪ እናደርጋለን። የእንግሊዝ መንግሥት ግን ይህ ሁሉ መረጃ በእጁ ውስጥ እያለ አምባገነኑን መለስ ዜናዊ እሹሩሩ ማለት መቀጠሉ በእጅጉ የሚያሳዝን ነው። የእንግሊዝ አገር ታክስ ከፋይ የድካም ውጤት ለመለስ ዜናዊ አምባገንና ዘረኛ አገዛዝ ማድለቢያ መዋሉ ኢትዮጵያዊያንን ብቻ ሳይሆን እንግሊዛውያንንም ጭምር የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ጉዳይ በመሆኑ፣ ዓይኑን ገልጦ እውነቱን ይጋፈጥ እንላለን። የአሜሪካ እና ሌሎች የአውሮፓ መንግሥታትም ፀረ-ህዝብ፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ዲሞክራሲ የሆነ የወንበዴዎችን ቡድንን በገንዘባቸው እየደጎሙ የወንጀል ተባባሪነታቸውን እንዲያቆሙ አበክረን እንጠይቃለን።

በዚያው ልክ ደግሞ በቢቢሲ ዘገባ ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የለንደን ኢምባሲ የወከለው "ከፍተኛ ዲፕሎማት" ዓይኔን ግንባር ያድርገው ዓይነት ቅጥፈት፤ በምስል ለቀረበው የሃገሩ ዜጎች ሰቆቃ አንዳችም ሃዘኔታ አለማሳየቱ፤ መለስ ዜናዊ በስሩ ባደራጃቸው እሱን የመሰሉ ጨካኞች እጅ መውደቋን እንድናይ አድርጎናል። ህዝብ በረሃብና በሰቆቃ በሚጠበስበት ወቅት በዓለም ፊት ለመዋሸት የመጣውን የወያኔ ካድሬና የበላይ ጌታውን መለስ ዜናዊን እናወግዛለን።

ይህ የመሰለው የመለስ ዜናዊ የሃሰት ድሪቶ መቀደድ አለበት። በየአገሩ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን የወገኖቻችንን ሰቆቃ ለየመንግሥታቱና ለህዝብ እንድናደርስ ጥሪያችን እናቀርባለን።

**ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የአለማቀፍ ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ የሚለግሱትበቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላር ለፖለቲካ ጭቆና እንደመሳሪያነት ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ያላለፉ ሴቶች እንደሌሉና ፣በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ስትሆን ተገዶ መደፈር የሚያስጨንቅ ጉዳይ አይሆንም ነበር ያለችው በተያያዘም የቢቢሲ ኒውስ ናይት ዘጋቢ ወደ ደቡብ አንድ መንደር ባቀናበት ወቅት በረሀብ ምክንያት አስር የሚሆኑ ሰዎች ህጣናትና አዋቂዎች ለሞት እንደተዳረጉና ህጣናትም በልመና ላይ እንደተሰማሩ መታዘብ ችልዋል ቢቢሲ ኒውስ ናይት በልዩ ዘገባው በሀገሪቱ የሚተገበሩት የልማት ፕሮግራሞችና እርዳታዎች የሚደርሱት የወያኔ ደጋፊዎች ለሆኑና ወያኔን ለመረጡ የህብረሰብ ክፍሎች ብቻ መሆኑን ለማረገገጥ ችልዋል።

ርሀብ በመጥናቱ የቡና ቅጠል እንደሻይ በማፍላት፣ለከብቶች የሚውለውን ምግብ ሳር ለልጆቹ እየመገብከዋቸው ነው ስትል የደረሰባትን ሰቆቃ የገለጠችው የችግሩ ሰለባ እማወራ ናት ካለችበት ቦታ በ 30 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በሚገኝ መንደር ውስጥ ለአራት ቀናት ያህል ሳይመገቡ የሰነበቱ ነዋሪዎች ደግሞ ከመንግስት ምንም ነገር እንደማይጠብቁ ነው የተናገሩት።

የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች በ 2005 ምርጫ ወቅት ከ አጥናፍ እስከአጥናፍ ለተቃዋሚ ፓርቲ ሙሉ ድምጣቸውን በመስጠታቸው እስከዛሬ ደረስ የመቀጣጫ እዳቸውን በስቃይ እየከፈሉት ይገኛሉ፣ ምንም አይነት የእህል ዘርም ሆነ ማዳበርያ ተከልክለዋል፣መረታቸውም ተወስዶባቸዋል። ከተቃዋሚ ሀይሎች ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በዚሁ ጉዳይ ላይ በሰጡት አስተያየት ሁሉም እርዳታዎች በወያኔ ቁጥጥር ስር እንደሆነ፣ማን ማግኘት እንዳለበትና እንደሌለበት የሚወስኑት አስተዳዳሪዎቹና ካድሬዎቹ እንደሆኑ፣ እርዳታውንም ለድጋፍ መሸመቻ ብሎም መያዣነት እየተጠቀሙበት እንደሆነ አስረድተዋል።

ፕሮፌሰር መራራ ጉዲናም በበኩላቸው በኢትዮጵያ ከፍተኛውን የህዝብ ቁጥር ይዞ በሚገኘው ኦሮሚያ ክልል ባለፉት ጥቂት ወራቶች ውስጥ ከ200 በላይ የሚሆኑ ሰዎች የኦነግ አባል፣ እነዲሁም አሸባሪዎች ናችሁ በመባል ያለምንም ፍርድ ለእስራት መዳረጋቸውንና በመቶዎች የሚቆጠሩት አሁንም በእስር ላይ እንደሚገኙ፣ ቶርች በመደረግ ላይ እነደሚገኙ ገልጠዋል።

በቅርቡ ከእስር ተለቆ በስደት ላይ የሚገኘው ግለሰብም በመንግሥት ወታደሮች በቁጥጥር ሥር ከዋለ ቦኋላ ወደ ማእከላዊ ወንጀል ምርመራ ተወስዶ ዘግናኝ የሆነ ድብደባ እንደተፈጸመበትና የወንድ ብሊቱን በመቀጥቀጥ የዘር ፍሬውን እንዳኮላሹ የሰጠውን ምስክርነት አቅርቦአል። በወያኔ ካድሬዎች የተሞላውና ወያኔ በዜጎች ላይ የሚፈጽማቸውን ሰቆቃዎች ለማስተባበል የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ተብዬው ድርጅት በቅርብ ባወጣው ሪፖርት በመላው ሀገሪቱ 35 እስረኞች ብቻ እንደሚገኙና በእስረኞቹ ላይ ተፈጸመ የሚባል ድብደባ ወይም ጭካኔ የተሞሉበት ኢ.ሰብአዊ ድርጊቶችና ቅጣቶች ስለመኖራቸው ምንም አይነት መረጃ እነደሌለ መናገሩን የቢቢሲው ጋዜጠኛ አጋልጦአል።

በሰበአዊ መብት ተሚጋችነታቸው እውቅናን ያተረፉት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምም በበኩላቸው ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጡ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በትክክል ህጋዊ ሆኖ እንዲሰራ ከተፈለገ አሁን በኮሚሽኑ ውስጥ እየሰሩ ያሉትን የወያኔ ካድሬዎች፣ ሙሉ በሙሉ በማውጣት በምትካቸው ለእውነት ስለእውነት ሊሠሩ የሚችሉና ለሰው ልጅ መብት ከበረታ ያላቸው በቂ እውቀትና ልምድ ባላቸው ሊተኩ እንደሚገባቸው መናገራቸውን ቢቢሲ ለአለም ህዝብ ይፋ ባደረገው ዶኩሜንታሪ ፊልም አቅርቦታል።

በእንግሊዝ የኢትዮጵያ ምክትል አምባሳደር አብዱረሺድ ዲላን በኢትዮጵያ ስላለው አጠቃላይ የሰብአዊ መብት ጥሰት ምን እንደሚል የቢቢሲ ኒውስ ናይት ጋዜጠኛ በጠየቀው ጊዜ፣ "ይህ ሪፖርት ተጨባጭነት የሌለው፣የዜናው ምንጮችም በምርጫው ወቅት በመላው ህብረተሰብ ተቀባይነት የተነፈጋቸው፣ የኢትዮጵያ ባላንጣዎች ናቸው፣ የኢት ጵያ መንገስት በህግ ነው የሚተዳደረው፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብትም በህገመንግስቱ የተረጋገጠ ነው" ሲሊ አይኔን ግምባር ያድረገው አይነት ክህደት ዐዘል ምላሽ፣ መስጠቱ ታውቆአል።

ኢትዮጵያ በየአመቱ ከምታገኘው 3 ቢሊዮን ዶላር ውስጥ 230፣000 ፓውንድ ያህሉ የእነግሊዝ ድርሻ ሲሆን ከዩ.ኤስ ቀጥላም ከፍተኛ እርዳታ ለጋሽ መሆንዋ ይታወቃል። በዚህ በያዝነው አመትም እንግሊዝ 290 ሚሊዩን ፓውንድ ለኢትዩጵያ እነደምትለግስ፣ ይህም ደግሞ ባለፈው ወር ይፋ የተደረገውን የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ 48 ሚሊዮን ፓውንድ ሳይጨምር መሆኑ ይታወቃል።

ይህ በዚህ እንዳለ የብሪቲሽ ብሮድካስቲንግ ሰርቪስ ቢቢሲ አረመኔውን የወያኔ አገዛዝ ያጋለጠበት ፊልም ለባለስልጣናቱ የእግር እሳት እየሆነ መምጣቱ ተገለጸ። ባለፈው ሳምንት በምህጻረ ቃሉ ቢቢሲ በመባል የሚታወቀው የብሪቲሽ ብሮድ ካስቲንግ ሰርቪስ ለአለም ህዝብ ይፋ ያደረገውና ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ከምእራባዊያን ለጋሽ ሃገራት በልማት ርዳታ ስም የሚያግበሰብሰውን በብዙ ቢሊየን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ በምን መልክ ኢትዮጵያዊያንን አፍኖና ረግጦ ለመግዛት እንዲሁም የተቃዋሚ ፓርቲ ዎችን እንቅስቃሴ ለማኮላሸት እያዋለው እንደሆነ በመረጃ ላይ የተደገፈው ፊልም እይታ የአገዛዙን ቁንጮዎች ጨምሮ ለበርካታ ባለስልጣናትና ሆድ አደሮች የእግር እሳት እየሆነ መምጣቱን ዘጋቢያችን ሰሞኑን ያሰባሰበውን መረጃ በመጥቀስ ገልጹአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ በተለያዩ ጉዳዮች ሲያደርግ እንደቆየው ሁሉ አሁንም ቢቢሲ ባቀረበው ተጨባጭ የሆነ መረጃና ዘገባ ላይ ጥላሸት የመቀባትና የመወንጀል ተግባሩን በስፋት መያያዙን፣ በተለይም በሃገር ውስጥ በቁጥጥሩ ስር በሚገኙት የሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና፣ ጋዜጦች ላይ ማደናገሪያ ጽሁፎችን በማጉረፍ ላይ መሆኑን አስታውቁአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ትብብር ለምን?

ወያኔ በአገራችንና በህዝባችን ላይ የፈጠረው የመበታተን አደጋ ለመቀልበስ በምትኩ ዘላቂ ሠላም፤ ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት በአገራችን ፓለቲካ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች ሁሉ ትብብር ፈጥረው በጋራ መታገል እንዳለባቸው ንቅናቄያችን ከተመሠረትበት ጊዜ ጀምሮ እያራመደ ያለ አቋም ነው። ከሁለት አመት በፊት በሳምንታዊው የግንቦት 7 ርዕሰ አንቀጽ በቁጥር 43 ላይ **“ትብብር ለምን**” በሚል ርዕስ የወጣው እንዲህ የሚል ነበር።

“የመተባበርን አስፈላጊነትና ጠቀሜታን ማንም አይስተውም፡፡ «ለአንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ»፣ «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር»፣ «ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ብርቁ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው» እነዚህንና ሌችም ምሳሌዎች የመተባበርን ጠቀሜታነት ማህበረሰባችን በቅጡ የተረዳ ለመሆኑ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

የመተባበርን ጠቀሜታ ለመረዳት ፖለቲካ ውስጥ መግባት አያስፈልገም፡፡የመለስ ዜናዊ አይነቱ በመንደር ዱርዬ መርህ የሚመራ እብሪተኛ የፖለቲካ ባላንጣ እንዲገጥመን የሚጠይቅ አይደለም፡፡ እንኳን አዋቂዎች ህጻናትም ሳይቀሩ በተናጠል ከሚሰሩት፣ ተባብረው የሚሰሩት ውጤት የማምጣት እድሉ የላቀ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡

በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ በተናጠል ከምንሰራቸው ስራዎች ይበልጥ መተባበርንና መደጋገፍን የሚጠይቁት ብዙዎች እንደሆኑ እናወቃለን፤፤ ከእነዚህ ጉዳዮች መሃል ፖለቲካ አንዱ ነው፡፡ ፖለቲካ ማህበራዊ እንቅስቃሴ አንደመሆኑ መጠን በጋራ የተሰባሰቡ ዜጎችን ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡ የግል ፖለቲካ ብሎ ነገር የለም፡፡ ለዚህ ነው ዜጎች ተደራጅተው ፖለቲካ የሚያካሂዱት፡፡ በተለይ ደግሞ ፖለቲካው መለስን የመሰለ ጉልበተኛ የገነነበት ሆኖ ሲገኝ ደግሞ፣ ይህን ጉልበተኛ ለመስታገስ የበለጠ ትብብር እንደሚያስፈለግ ገልጽ ነው፡፡ ስለእዚህ ዛሬ የሃገራችን ፖለቲካ ያለበትን ችግር ለመቅረፍ፣ በአምባገነነንት ምትክ ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት ለመገንባት የመለስ ዜናዊን እብሪት አምረው የሚጠሉ ተባብረው የመስራታቸው አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ነው፡፡ ስለእዚህም ነው ግንቦት 7 የመተባበርን አስፈላጊነት ለማስረዳት የምናጠፋውን ግዜ፣ ትበብር ለምንና እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች ለማንሳትና ምልሻቸውን ለመስጠት ልናጠፋው ይገባል የሚለው፡፡ ትኩረታችንን ሊስብ የሚገባው፣ ትብብሮች እንዴት ሊፈጠሩ ይችላሉ? ከተፈጠሩም በኋላ ተጠናክረው እንዴት ይቀጥሉ? የትብብሮች መነሻና መድረሻ ምን ይሁን? የሚሉት ጥያቄዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የመለስ ዜናዊን አምባገነንነት መጥላት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ መለስ ዜናዊ በፈጠረው አምባገነናዊ ስርአት ምትክ ምን እንተካ የሚል ጥያቄ ማንሳት፣ ይህንን ስርአት በምን ሂደት አልፈን እናምጣው፣ የተለያ የፖለቲካ ድርጅቶች የስራ ሃላፊነት ምን ይሆናል የሚሉትን አስቸጋሪ ጥያቄዎች መመለስ ይጠይቃል፡፡

ለእዚህም ነው ግንቦት 7 ገና እንደ ንቅናቄ ሲጸነስ የመተባበርን አስፈላጊነት መስበክ ብቻ ሳይሆን፣ ትብብር ከማን፣ ለምንና አንዴት የሚሉትን ጥየቄዎች በማንሳት የማያሻማ ምላሽ የሰጠው፡፡

ለመተባበርና ተባብረንም ለመዝለቅ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊደግፏቸው የሚችሉ ከውዝግብ ነጻ ከሆኑ መሰረታዊ የመተባበሪያ ነጥቦች ያስፈልጋሉ ከሚል እምነት በመነሳት ግንቦት ሰባት የሚቀጥሉትን ቁም ነገሮች አስቀምቷል፡፡

1. መለስ ዜናዊ ሳይገደድ ወይም ሳይወገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት አይቻልም
2. የመለስ ዜናዊንና ጥቂት ግብረ በላዎቹን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ የሚሰባሰቡ ሃይሎች በሃገራችን በሰፈነው አምባገነናዊ ስርአት ምትክ የሚተኩትና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት የሚገነባበት ኢትዮጵያ የምንላት አንዲት ምሉእና ልኡዋላዊ ሃገር መሆኗን መግባባት ይኖርባቸዋል። ይህ ትብብር መለስን አስገድዶ ወይም አስወግዶ በዘረኛ አምባገንንን የፖለቲካ ስርአት ምትክ ስለሚተካው የፖለቲካ ስርአት የጋር ስምምነት ሊኖረው ይገባል፡፡

ይህም የፖለቲካ ስርአት የጥቂት ምርጦች መንግስት ሳይሆን፣ ህዝብ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የሰየመው መንግስታዊ አስተዳደር ይሆናል፡፡ ከእዚህ በላይ የቀረቡት ሶስት ነጥቦች ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ለመተባበር በቅድሚያ ሊስማሙባቸው የሚገቧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ግንቦት 7 እነዚህ ብቻቸውን ለመተባበር በቂ ናቸው የሚል እምነት የለውም፡፡ መተባበሩ እንዲዘልቅና የሚተባበሩት ሃይሎችም በመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ እግር ለመተካት የሚመኙት በምርጫ የሚመጣው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ህልም እንዲሰምር፣ ይህ እንዴት እውን ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ በመንሳት በምላሹ ዙሪያ አስቀድመው መስማመት አለባቸው፡፡

ግንቦት 7 በእዚህም ነጥብ ዙሪያ ግልጽ አቋም ወስዷል፡፡ የግንቦት 7 አቋም በዋንኛነት የመነጨው የኢትዮጵያ ህዝብ በ1997 ምርጫ ያሳየውን የፖለቲካ ብስለት፣ ለመብቱ መከበር የከፈለወን መስዋእትነት፣ ይህ መስዋአትነት የታለመለት ግብ እንዳይመታ ካደረጉት ምክንያቶች የሚመነጭ ነው፡፡ በመሆኑም የሚቀጥለው መንግስታዊ አስተዳደር በህዝብ ነጻና ፍትሃዊ የምርጫ ተሳትፎና ውሳኔ ሊመጣ የሚገባው መሆኑን የተግባቡ ሃይሎች ለመተባበር ከሚስማሙባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱና ቁልፉ ይህንን አይነቱን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በሃገራችን አንዴት እውን ማድረግ ይቻላል የሚለው ነው፡፡

ግንቦት 7 ለእዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ነፃ የፍትህ ስርአት፣ ከፖለቲካ ያልወገነ የመከላከያ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል፣ ነጻ መገናኛ ብዙሃን፤ ከየትኛውም ምርጫ በፊት በሃገራችን ሊኖሩ ይገባል የሚለውን ነው፡፡ በእዚህ ላይ ስምምነት ሳይያዝ የሚፈጠር እውነተኛ ትበብር ሊኖር አይችልም፡፡ ትብብር ቢኖርም ህዝብን ያላሳተፈ የምርጦች ትብብር ብቻ ነው መሆን የሚችለው፡ህዝብን የሚጠቅም ዘለቄታነት ያለው ትብበር ከቶውኑ ሊሆን እንደማይችል ግንቦት 7 ጽኑ እምነት አለው፡፡

በመጨረሻም፣ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የመተባበሪያ ምእራፎች ላይ መግባባት ከተደረሰ በኋላም ይህን ስምምነት እንዴት በጋራ በተግባር እናውለዋለን በሚለው ጉዳይ ላይ ተጨማሪ የጋራ ግዛቤ ሳይኖር ትብብሩ የትም ሊደርስ እንደማይችል ግንቦት 7 ያምናል፡፡ መለስን አስገድደው ውይም አስወግደው ነጻ ተቋማት በመገንባት፣ በህዝብ ምርጫ የሚሰየም መንግስታዊ አስተዳደር ለመመስረት የተስማሙ ሃይሎች፣ ይህንን አንዴት ተግባራዊ ለማድረግ አንደሚችሉ አስቀድመው ጥያቄ ማንሳት ይኖርባቸዋል፡፡ እዚህ ላይ ለማንሳት የተፈለገው የሚተባበሩትን ሃይሎች የትግል ስልት አይደለም፡፡ አምባገነናዊውን ስርእት አስወግዶ ህዝብ በምርጫው በሚሰይመው ስርአት መመስረት መሀል የሚፈጠረውን የስልጣን ክፍትት እንዴትና በምን እንሙላው የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት ብቻ ነው፡፡

ግንቦት 7 ለእዚህም ጥያቄ የማያሻማ መልስ ሰጥቷል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ መቋቋም ስለሚገባው፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስለሚሰየም መንግሰት ስምምነት የደረሱ ሃይሎች፣ ይህንን ስምምነታቸውን ማስፈጸም የሚችሉባቸውን ነጻና ገለልተኛ መንግስታዊ ተቋማት ለመገንባት አንድ አይነት የጋራ የሽግግር መንግስት ማቆም እንደሚኖርባቸው ግንቦት 7 በግለጽ አስቀምጧል፡፡ የእዚህ መንግስት ዋንኛ ተግባርም፣ ህዝብ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በአስቸኳይ አድርጎ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በታሪካችን ለመጀመሪያ ግዜ የሚደረግ የስልጣን ርክክብ ለማድርግ እንደሆነ ግንቦት7 አስምሮበታል፡፡ ይህ የሽግግር መንግስት ምን አይነት ቅርጽ ይኖረዋል ለሚለው ጥያቄ መልሱን የተባበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች በሚጠሩት ታላቅ ሸንጎ የሚወሰን ይሆናል የሚል አቋም ግንቦት ወስዷል፡፡

የተረጋጋ ሽግግር ለመፍጠር ግን ይህ ውይይት በሰለጠነና አምክህዮታዊ በሆነ መንገድ ከአሁኑ መጀመር ይኖርበታል፡፡

በግንቦት 7 በኩል ስለመተባበር አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ትብብር ለምንና እንዴት ለሚሉት ጥየቄዎች መልስ ሰጥተናል፡፡ የሃገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ስለትበብር አስፈላጊነት ሲያትቱ በተመሳሳይ ትብብር ለምንና እንዴት የሚለውን ጥያቄ አንስተው መልስ ቢሰጡ የሃገራችንን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ህዝብም በየግዜው የፖለቲካ ድርጀቶቹ ለሚያወሩት የመተባበር አስፈላጊነት ድጋፉን መስጠት የሚችለው ይህ ትብብር ለኔ ምን ይፈይዳል ለሚል ጥያቄው መለስ ካገኘ ብቻ ነው፡፡ ከእዚህ ውጭ በመተባበር ስም የሚፈጠሩ ግንባሮች ቅንጅቶች፣ ምድረኮችና ህብረቶች ከእዚህ ቀደም ተፈጥረው ከነበሩ ፍጻሚያቸው ሳያመር ከከሰሙት ትበብሮች አሳዛኝና አሳፋሪ እጣ የተሻለ እድል ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ስለእዚህም ነው፣ ግንቦት 7 ስለመተባበር አስፈላጊነት ድምጻቸውን አጉልተው ለሚጮሁ ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች በሙሉ የመተባበሪያ አጀንዳቸውን ለህዝብ ግልጽ እንዲያደርጉና ህዝብም በእነዚህ በጋራ ሁላችንም በምንስማማባቸው ነጥቦች ዙሪያ ድጋፍ እንዲሰጠን በጋራ ጥሪ እናደርግ የሚለውን የራሱን ጥሪ በወገናዊ ስሜት የሚያቀርበው፡፡”

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የአለማቀፍ ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ የሚለግሱትበቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላር ለፖለቲካ ጭቆና እንደመሳሪያነት . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

የወያኔ የፕሮፓጋንዳ ማሽን የሆነውና ህዝብን በማደንቆር የሚታወቀው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን \ቢቢሲ ዘገባውን ያጠናቀረው የኢትዮጵያ ጠላት የሆኑ ክፍሎችን ብቻ በማነጋገር እንደሆነ\ እየወተወተ ሲሆን፣ በተለይም የወያኔን አገዛዝ የሚደግፉና ፕሮፓጋንዳውንም ለማራገብ ራሱ ወያኔ የቀፈቀፋቸው ድረ ገጾች ቢቢሲ እንዲህ አይነት የስም ማጥፋት ስራ የጀመረው ዛሬ ሳይሆን፣ ከበርካታ አመታት በፊት እንደነበረ፣ አሁንም ቢሆን የወጣው ቪዲዮ ሃገሪቱ እያሳየች ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማደናቀፍ ታስቦና ከለጋሽ ሃገራትም በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሚለገሰውን ገንዘብ ለማገድ ነው በማለት ቅጥ ያጣና የተዘባረቀ ጽሁፍ እያአወጡ መሆኑን ገልጹአል።

ሪፖርተራችን ለዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ቅርብ የሆኑ የውስጥ ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው፣ በተለያዩ አጀንዳዎች ተወጣጥረው የሚይዙ የሚጨብጡትን ያጡት ዘረኞች የአሁኑ የቢቢሲ ሪፖርት ከፍተኛ የራስ ምታት እንደሆነባቸውና፣ ይህን ይፋ ዘገባ ደብዛውን የሚያጠፋ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማጡአጡአፍ እየተሩአሩአጡ እንደሆነ ታውቁአል።

ቢቢሲ ለአለም ህዝብ ይፋ ባደረገው በዚሁ ቪዲዮ ጋዜጠኞቹ በኦጋዴን፣ በባሌ፣ በወላይታ፣ በደቡብና ምዕራብ ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ በመዘዋወር ኢትዮጵያዊ ድሃ እየደረሰበት ያለው ዘግናኝ ሰቆቃ በገዛ ዓይኖቻቸው መመልከታቸውን የገለጸ ሲሆን በተለይም፣ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታን ሳይጨምር ለልማት እየተባለ ከምዕራባዊያን በየዓመቱ የሚጎርፈው 3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለትም አምሳ አራት ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ እንደፈለጉ እንደሚያዙበት ማረጋገጡ ይታወቃል።

የቢቢሲ ጋዜጠኞች ዘረኛውን አምባገነን መለስን አልደገፉም የተባሉ ነዋሪዎች መሰረታዊ የሆኑ የምግብና የውሃ አቅርቦት እርዳታ መነፈጋቸውና በዚህም ምክንያት አዋቂዎች ሳይቀር በረሃብ መሞት መጀመራቸው ቦታው ድረስ በመሄድ በዓይኖቻቸው ማየታቸውን፤ መለስን ያልደገፉ ገበሬዎች ማዳበሪያም ሆነ ምርጥ ዘር እንደማያገኙ ከገበሬዎቹ አንደበት መስማታቸውን፤ ወጣት ሴቶች ብቻ ሳይሆን በእድሜ የገፉ እናቶች፣ አያቶች፣ ነፍሰጡሮች ሳይቀር በወታደሮች መደፈራቸውን ከበደሉና ግፉ ቀማሾች አንደበት መስማታቸውን የገለጹ ሲሆን ሰቆቃ የተፈፀመባቸው፤ ተዘቅዝቀው የተሰቀሉ፣ ብልታቸውን የተኮላሹ ወንዶችን ማነጋገራቸውን መግለጻቸው ይታወሳል።

## ለእርዳታ የሚሰጠው ገንዘብ በአገራችን ለፖለቲካ ጭቆና መዋሉን ቢቢሲ ማጋለጡን ተከትሎ የወያኔ ሹሞች ስለሚወስዱት እርምጃ እየተነጋገሩ እንደሆነ ታወቀ። በምስጥራዊ ስብሰባ ላይ የሰነበቱት የወያኔ አምባሳደሮች ዋና ተግባራቸው ይህንን ማስተባበር እንደሆነ ተነግሮአቸዋል ተባለ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከምዕራባዊያን ሃገራት በልማት ርዳታ ስም የሚያግበሰብሰውን በቢሊየን የሚቆጠር ዶላር ገንዘብ ተቃዋሚ ሃይሎችን ለመጨፍለቅ እንዲሁም የራሱን ደጋፊዎች ለማበራከት እየተጠቀመበት መሆኑ በይፋ ያጋለጠው የቢቢሲ ዶክሜንታሪ ፊልም እይታ የዘረኛውን አገዛዝ ባለስልጣናት እጂግ ማደናገጡን የውስጥ ምንጮቹን በመጥቀስ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት አመለከተ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ቢቢሲ ለአለም ህዝብ ይፋ ያደረገው የሰቆቃ ሪፖርት ባለፈው ሳምንት ከመላው አለም ተጠርተው የአባይ ግድብ ግናባታ ዜና ለምን በውጪ የሚገኘውን ህብረተሰብ እንዳላንቀሳቀሰና ወያኔ በዲያስፖራ ክፍሉ አማካይነት ለመስራት ያቀደው ሥራ ያልተሳካበትን ምክንያት ለመገምገም ምስጥራዊ ስብሰባ ተቀምጦ የነበረውን የወያኔ አምባሳደሮች ቡድን ትኩረት ለውጦ እንደሰነበተ ለማወቅ ተችሎአል። ቢቢሲ ዘጋቢዎቹን በስውር አገር ውስጥ አስገብቶ የሰቆቃ ሰለባ የሆኑትን ሰዎችና ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን በምስጥር በማነጋገር ለአለም ህዝብ ይፋ ባደረገው በዚህ የሰቆቃ መረጃ ወያኔ ላለፉት 20 አመታት በምዕራባዊያን ሊጋሮቹ አዕምሮ ገንብቶት የኖረው የተሳሳተ የፖለቲካ ተከለሰውነት አፍር ከዲሜ እንደበላ በርካታ ፖለቲካ ተንታኞች እየተናገሩ ነው።

ይህንን አስመልክቶ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ያነጋገረው ዘጋቢያችን በቢቢሲ ጋዜጠኛ ስራ እጂግ መደሰታቸውንና መኩራታቸውን ገልጸ ፣ ምንም እንኳን ምእራባዊያን የወያኔን አገዛዝ ተግባር አንጠርጥረው የሚያውቁ ቢሆንም እንዲህ አይነት ግፎች በመረጃ ተደግፈው ሲቀርቡ በየሃገራቱ የሚኖረው ታክስ ከፋይ ህዝብ በዝምታ ሊያልፋቸው ስለማይችል እስከዛሬ በአገራችን ላይ ይከተሉ የነበረውን የተሳሳተ ፖሊሲ ለመመርመር የሚረዳ ሥራ ለምስራት ይረዳል ማለታቸውን ገልጾአል።

ቢቢሲ ባለፈው ሃሙስ ሃምሌ 29 ቀን ምሽት ለህዝብ ይፋ ባደረገው ወያኔ ሠራሽ ሰቆቃ ሪፖርት ላይ የሚወከለውን የወያኔ አገዛዝ ሰቆቃ ወነጀል ማስተባበል ተሰኖት ሲደነባበር የነበረው በሎንዶን የወያኔ ምክትል አምባሳደር የሆነ ግለሰብ፣ ሪፖርቱን ሽብርተኛ ያላቸው ኦብነግ እና ኦነግ በሰጡት የሃሰት ምስክርነት ቃል ላይ ተመስርቶ የወጣ ነው በማለት ለማናናቅ ከመሞከር አልፎ በአገራችን ለተከሰተው ረሃብ አለም አቀፍ ህብረተሰብ የልገሳ እጁን እንዳይዘረጋ ለማሰናከል የተቃጣ እርምጃ ነው በማለት በማግሥቱ ሃምሌ 30 ቀን በጽሁፍ ባወጣው መግለጫ ቢቢሲን ለመወንጀል ሞክሮአል።

በአገር ውስጥ ለሚደረገውን ህዝባዊ ተቃውሞ ጎሬቤት ኤርትራን መወንጀል የዕለት ተዕለት ተግባሩ የሆነው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ፤ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋቾችና ጋዜጤኞች የሚጋለጡትን ተመሳሳይ ሰቆቃዎችን በምርጫ 97 የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ በነበሩትና ለሰው ልጆች ሁሉ እኩልነትና ነጻነት ተቆርቋር መሆናቸውን በተግባር ባስመሰከሩ ክብርት ማዳም አና ጎመስ ላይ ማላከክ የተለመደ አድርጎታል።

ቢቢሲ ባለፈው ሃሙሱ የኒውስ ናይት ፕሮግራም ዝግጅቱ ወያኔ ከምዕራባዊያን በሚያገኘው በቢሊየኖች የሚቆጠር የርዳታ ገንዘብ እንዴት አድርጎ ህዝብንና ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን እንደሚያፍንና እንደሚጨቅን ያጋለጠው የቢቢሲ ዶክመንተሪ ፊልም በውጪ ሃገራት በሚገኙ የኢትዮጵያዊያን የመረጃ ድረ ገጾች ሁሉ ላይ እየተሰራጨ ሲሆኑ ኢትዮጵያዊያኑ የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታት በሚሰጡት የእርዳታ ገንዘብ በህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ወንጀል እንዲረዱ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ የዲፖሎማሲ ዘመቻ ለመጀመር የሚያስችል ዝግጅት እያካሄዱ እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ ያመለክታል።

### የኦነግና ኦብነግ ህብረ ብሄር ከሆነው ግንቦት 7 ጋር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በኦሮሚያ ክልል ተወላጅ ከሆኑት ወጣቶች የተገኘው አስተያየት በአብዛኛው በኦነግ ተጠርጣሪነት ስም በክልሉ ዜጎች ላይ እየተፈጸመ ያለው ሰቆቃ በአገሪቱ ታሪክ በየትኛውም ጨቋኝ አገዛዞች ይደርስ ከነበረው እጅግ የከፋ እንደሆነ በዚህም ምክንያት ህዝብ ወያኔን አጥብቆ ለመታገል ከምንጊዜውም በላይ ቆራጥነት እንዳለው የሚያረጋግጥ ነው። በአገር ውስጥ የኦሮሞን መብትና ጥቅም እናስጠብቃለን በማለት የምንቀሳቀሱ ድርጅቶች እንደማገኛቸውም የአገሪቱ ተቃዋሚ ወያኔ የጣለባቸውን የፍርሃት ቆፈን ተቋቁመው ለነጻነታችን ሊያታግሉን አልቻሉም የሚሉት እነዚህ የኦሮሚያ አካባቢ ወጣቶች በተስፋ የምንጠብቀው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ግንቦት 7ን ከመሰለ የአገሪቱን የዲሞክራቲክ ሃይሎችን ካሰባሰበ ድርጅት ጋር ግንባር ለመፍጠር እንቅስቃሴ መጀመር የህዝባችንን ስቃይና መከራ ለማስቆም ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው እንደሚያምኑ ተናግረዋል። በቅንጅት ጊዜ ቅንጅቶችን የነፍጠኛ ሥርዓት ሊመልሱብህ ነው ተብሎ በክልልላችን የተነዛው ፕሮፖጋንዳ አዘናግቶን ነበር ያሉት የኦሮሚያ ወጣቶች ወያኔ ከአሁን ቦኋላ እንደያኔው አይናችንን እራሱ ከሚያደርስብን ግፍና መከራ ሊነቅል ወይም ሊከፋፍለን የሚችል ፕሮፖጋንዳ ሊሠራብን አይችልም ይላሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት አዲስ አበባ የሚገኘውን ዘጋቢዉን ዋቢ በማድረግ እንደዘገበው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ መምህር የሆኑ አንድ ምሁር በአሁኑ ጊዜ ባለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድባብ ሰፊ ሕዝብ ያላቸውን አማራና ኦሮሞን በነፍጠኝነትና በነፍጠኛ ተጎጂነት ፈርጆ ከፋፍሎ መግዛት የአገልግሎት ዘመኑ እንዳለፈበት የሚያሳዩ ምልክቶች መታየት ጀምረዋል ማለታቸውን ገልጹአል።

ምሁሩ እንደገለጹት ጎጠኛው የወያኔ አገዛዝ ላለፉት ሃያ ዓመታት የኦሮሞ ሕዝብ ከኦህዴድ ሌላ አማራጭ አገር ብሄራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንዳይከተል የኦሮሞን ሕዝብ ሲያስፈራራበት ከነበሩት መካከል፣ ነፍጠኛው ተመልሶ በእጅ አዙር መጣልህ፣ በትውልድ ሥፍራህ ላይ እንደገና ሊገዛህ ነው፣ በኢህአዴግ የተመሠረተው የፌዴራል ሥርዓት ያስገኘልህን ራስን በራስ የማስተዳደር መብትህን ነጥቆህ ወደ አሃዳዊነት አገዛዝ መልሶ ቋንቋህን አሳጥቶ ሊገዛህ ነው የሚሉ እንደነበሩ አስታውሰዋል።

በሂደት የኦሮሞ ሕዝብ የተረዳው ተጨባጭ ግንዛቤ ግን ዘመነኛው ነፍጠኛ የአማራ ገዢ መደብ ሳይሆን በህወሃት የበላይነት የሚመራው- ወያኔ ኢህአዴግ መሆኑን ነው ያሉት ምሁሩ ፣ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ ሃቀኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘር፣ በብሄር፣ በጎሳ፣ በቀበሌ ፣ በሃይማኖት ሳይከፋፈሉ በአንድነት ተጠናክረው የጠራ የጋራ የፖለቲካ ፕሮግራምና ጥንካሬ ተላብሰው በኦሮሚያ ውስጥ ቢንቀሳቀሱ ከወትሮው የላቀ ከፍተኛ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ ብለዋል። ምክንያታቸውንም ሲያስረዱም ህብረተሰቡ ላለፉት ሃያ ያመታት የመንግሥትን ባዶ ፕሮፓጋንዳዎችን እና ተጨባጭ ድርጊቶችን ተመልክቶ ለውጥ ለማምጣት በአንድነት መቆም እንደሚያስፈልግ ተረድቷል ማለታቸውን ኢሳት ዘግቡአል።

በግንቦት7፣ በኦነግ፣ በኦብነግና በሌሎችም ድርጅቶች መካከል በጋር ለመስራት የተጀመረው ጥረት የሰሞኑ ዋነኛ መነጋገሪያ መሆኑን የገለጸው የኢሳት ዘጋቢ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የኦህዴድ ባለስልጣናት ለካድሬዎቻቸው ኦነግ ከነፍጠኞች ጋር እያበረ ነው የሚል ቅስቀሳ መጀመራቸውን፣ በህዝቡ በኩል የሚታየው ስሜት ደግሞ ተቃራኒው መሆኑን መግለጹ ታውቁአል።

### በኢትዮጵያ የዋጋ ንረትን መቆጣጠር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የዚህ የዋጋ ንረት ተጎጂ የሆነው በድህነት እየማቀቀ የሚገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ በምግብ ዋጋ ላይ የሚታየው ንረት ኑሮን ፍጹም መቋቋም ከማይቻልበት ደረጃ ላይ እንዳደረሰው እየገለጸ ባለበት ባሁኑ ወቅት የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናትና ጥቂት ደጋፊዎቻቸው ከህዝብ ያግበሰበሱትን በቢሊየን የሚቆጠር ገንዘብ አሁንም እንደፈለጉ እየጨፈሩብትና የሚጥሉበት አጥተው እንደሚገኙ የአይን እማኞች እየገለጹ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዘም ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በሁለት ዲጂት እያደገ ነው እያለ ሲሆን የአለም የገንዘብ ድርጅት የኢትዮጵያ የቀጣዩ አመት እድገት 7.5 ከመቶ እንደሚሆን ቀደም ብሎ መግለጹ ይታወሳ።

በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ ቀንድ ባለፉት 60 ዓመታት ያልታየ ድርቅ መከሰቱና ከዚህም ተጎጂ ህዝብ ውስጥ አብዛኛው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኝ የተዘገበ ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንደሚለው ኢትዮጵያ ውስጥ እርዳታ የሚያገኙ 13 ሚሊዮን ዜጎች አሉ ማለቱ ይታወቃል።

### ሱዳን በተባበሩት መንግስታት ሄሊኮፕተር ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የተባበሩት መንግስታት ጦር ባለስልጣን ለቢቢሲ እንደተናገሩት ፍንዳታው የደረሰበት ቦታ ሄሊኮፕተተራችን በጊዜ ፈጥኖ የደረሰ ቢሆንም ከቦታው ለቀን መነሳት አልቻልንም፣ ለዚህም ዋናው ምክንያት የሱዳን ወታደራዊ ሃይል ተኩስ እንደሚከፍትብን በማስጠንቀቁ ነበር ካሉ በሁኣላ፣ ማንም አካል የጦር ሄሊኮፕተሩ በወቅቱ ባለመንቀሳቀሱና የሶስቱ ወታደሮች ህይወትም በማለፉ እኛን ሊጠይቀን አይገባም ብለዋል።

ከ4200 በላይ የሚሆን የኢትዮጵያ ጦር ሱዳን ውስጥ በአቢየ ክፍለ ግዛት የሰፈረው በቅርቡ ሲሆን ጦሩ በሰፈረ በአጭር ጊዜ ውስጥ አደጋ ሲገጥመው የአሁኑ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። የፍንዳታ አደጋው የደረሰበት የአቢየ ግዛት ክፍል በሱዳን መንግስት ታማኝ ወታደሮች ቁጥጥር ስር ይገኝ እንደነበር የቢቢሲ ዘገባ አክሎ አመልክቱአል።

ሰሜን ሱዳን ቀደም ብላ የኢትዮጵያ ጦር አቢየ ግዛት ውስጥ እንዲሰፍር ስምምነት ያደረገች መሆኑ ቢታወቅም፣ የጦር ሃይሉ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ትእዛዝ የሚንቀሳቀስ ከሆነ የገባሁትን ስምምነት አፈርሳለሁ ማለቱአና በአካባቢው በሰፈረው የኢትዮጵያ ጦር ሃይል ላይ ያላትን ተቃውሞ በተዘዋዋሪ መንገድ መግለጹአን ቀደም ብለን መዘገባችን አይዘነጋም።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ**:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org